# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ – አጭር ማጠቃለያ በቀላል ቋንቋ

**<u>የቀረበ የገንዘብ ድጋፍ</u>**፦ የ Valley Medical Center & Clinics በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው መሠረት ለድንገተኛ አደጋ ወይም ለሌሎች አስፈላጊ የሕክምና እርዳታዎች ገንዘብ መክፈል ለማይችሉ የብቁነት መስፈርቱን ለሚያሟሉ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። Valley Medical Center & Clinics ለማንኛውም አጠቃላይ የቤተሰቡ ገቢ የፌደራል የድህነት ደረጃ (FPL) 400% ድረስ ለሆነ እና ማንኛውም የሶስተኛ ወገን ሽፋን ጥቅም ላይ ውሎ ካለቀ በኋላ፣ ለታካሚ/ለዋስትና ሰጪ አካል የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። በ Valley Medical Center & Clinics ላሉ ተቋማት እና/ወይም ሙያዊ አገልግሎቶች፦

- የ FPL ከ 0% - 300% ለ 100% የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ

ከህክምና የመውጫ ቀናቸው በጁላይ 1 ፣ 2022 ወይም ከዚያ በኋላ ለሆኑ፣ በ Valley Medical Center & Clinics ውስጥ ለሚሰጡ ተቋማዊ አገልግሎቶች ብቻ፦

- የ FPL ከ 301% - 350% ለ 75% የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ
- የ FPL ከ 351% - 400% ለ 50% የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ

የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆነ ግለሰብ በአብዛኛው ለአስቸኳይ ወይም ለሌሎች አስፈላጊ የሕክምና እርዳታዎች ከሚጠየቀው ገንዘብ የበለጠ ገንዘብ ሊከፈልለት አይችልም።

**<u>የብቁነት መስፈርቶች እና የሚቀርበው እርዳታ</u>**፦ ለለገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆን በሚያስፈልገው ሁኔታ እና እንክብካቤ ሁኔታ፣ የመድሕን ሽፋን ወይም ሌሎች የክፍያ ምንጮች፣ የገቢ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ እና ታካሚው ወይም አቅራቢው ከግምት ውስጥ መግባት በሚፈልጓቸው ማናቸውም ልዩ ጉዳዮችን ጨምሮ በብዙ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

የገንዘብ ድጋፍ የሚፈልጉ ታካሚዎች በገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ሂደቱ መሰረት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ይህም የታካሚውን W-2 መግለጫን፣ ወቅታዊ የደመወዝ መክፈያ ስሊፕን፣ የባንክ ሒሳብ መግለጫዎችን ወይም የባለፈው ዓመት የገቢ ግብር መክፈያ <u>ማቅረብን እንዲሁም</u> በዋሽንግተን ግዛት የገንዘብ ድጎማ የሚደረግበት የጤና እንክብካቤን ጨምሮ ለሁሉም የእርዳታ ምንጮች የሚቀርብ የማመልከቻ ሂደቱን ማጠናቀቅን ይጨምራል።

**<u>እርዳታ ለማግኘት እንዴት ማመልከት ይቻላል</u>** ታካሚው ወይም በታካሚው እንክብካቤ ላይ ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም ሰው፣ ይህም የቤተሰቡን አባል ወይም አገልግሎት አቅራቢን ጨምሮ ገንዘብን በተመለከተ ያሉባቸውን ችግሮች ማቅረብ ይችላሉ። ከዚያም ታካሚው ወይም ኃላፊነት የሚሰማው ወገን የገንዘብ ድጋፍድጋፍ ማመልከቻውን ሞልቶ እንዲያጠናቅቅ ይበረታታል። የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት፣ አንድ ሂሳብ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከመቀበሉ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል።

**<u>ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆን ማለት ምንድን ነው</u>**፦ የገንዘብ ድጋፍ በ Valley Medical Center & Clinics ለሚሰጥ የሕክምና ክትትል ብቻ የሚቀርብ ነው። እንደ የጉዞ፣ ምግብ፣ ማረፊያ፣ እና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሣሪያ እና ለመሳሰሉት የሚወጡ ወጪዎች በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው አይሸፈኑም። በValley Medical Center & Clinics አቅራቢ ከተፃፈ እና በValley Medical Center & Clinics ፋርማሲ (ካለ) ከተሞሉ የመድሃኒት ማዘዣዎች ለ100% የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ ከFPL እስከ 300% ያህል ለታካሚዎች ሊሸፈኑ ይችላሉ።

**<u>ቅጂዎችን የት ማግኘት እንደሚቻል፣ ሰነዶችን ገቢ ማድረግ እና የእውቂያ መረጃ</u>**፦ የ Valley Medical Center & Clinics የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ፣ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ፣ በቀላል ቋንቋ የቀረበ አጭር ማጠቃለያ ፣ እና የሂሳብ አከፋፈል እና የመሰብሰብ ፖሊሲዎች ከክፍያ ነጻ የሚቀርቡ ናቸው። እነዚህ ሰነዶች በኦንላይን፣ በስልክ፣ ወይም በአካል በበርካታ ቋንቋዎች ሊገኙ ይችላሉ። ሰነዶቹን ለማውረድ ወይም ለማተም በኦንላይን በ valleymed.org/financialassistance ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም አንድ ቅጂ እንዲሰጥዎ በአካል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ።

የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ እና በእንግሊዝኛ ወይም በስፓኒሽኛ የድጋፍ ሰነዶችን ለማግኘት፣ አሁን ላይ የእርስዎን ሰነዶች ገቢ ለማድረግ MyChart ን መጠቀም ይችላሉ። ሌሎች ማመልከቻዎችን በሙሉ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በአካል ገቢ ማድረግዎን ይቀጥሉ። ግምት ውስጥ ለመግባት የቀረበው ማንኛውም መረጃ በጤና ኢንሹራንስ ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (Health Insurance Portability and Accountability Act (HIPAA)) መሰረት እንደ የተጠበቀ የጤና መረጃ ይቆጠራል።

| Valley Medical Center & Clinics | Valley Medical Center & Clinics |
|---|---|
| Patient Financial Services<br>P.O. Box 59148<br>Renton, WA 98058-2148<br>ስልክ 425.690.3578<br>ፋክስ 425.690.9578<br>ሰኞ-ዓርብ 8:00 a.m. – 5:00 p.m.<br>mychart.valleymed.org/#mychart | Patient Financial Services<br>3600 Lind Ave SW, Suite 110<br>Renton, WA 98057-4970<br>ስልክ 425.690.3578<br>ፋክስ 425.690.9578<br>ሰኞ-ዓርብ 8:00 a.m. – 5:00 p.m.<br>mychart.valleymed.org/#mychart |